የሰ/መ/ቁ. 81405

ጥር 29 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ መሐመድ ሲራጅ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የአወሊያ ዋና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ነ/ፈጅ አቶ አሕመድ ሙዲ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

አመልካች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2(1) መሠረት የስራ መሪ በመሆናቸው ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የሚዳኝ አይደለም የሥራ ክርክር ችሎቱም ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ እና በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የቀረበለትን ይግባኝ ዘግቶ በማሰናበት የፌ/ከ/ፍ/ቤት ስራ ክርክር ችሎት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆኑ ሊታረሙ ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርመሮ አመልካች በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 እና በማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/1/ መሠረት በሰራተኛ ውስጥ የሚካተት ሳይሆን የስራ መሪ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ሊስተናገድ አይገባም የመባሉን አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ክርክር ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አመልካች ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የሚስተናገድ አይደለም በማለት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሐግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች በ07/03/04 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረቡት ክስ ይዘት ተጠሪው ድርጅት በሕግ አማካሪነት ቀጠሮ ሲያስራኝ ከቆየ በኋላ አላግባብ ከስራ ያሰናበተኝ በመሆኑ የስራ ውሉ መቋረጥ ሕገወጥ ነው ተብሎ ተጠሪው የካሣ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ፣የስራ ስንብት ክፍያ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት ያደረጉት ክፍያ ለጠቅላላ ሰራተኛ የተሰጠውን የ40% የደመወዝ ጭማሪ እና መሰል ክፍያዎችን እንዲከፍለኝ ውሳኔ

ይሰጠኝ የሚል እና  የአዋጅ ቁጥር 377/96  ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች  ውሳኔ የሰጡት አመልካች የስራ መሪ በመሆናቸው  ጉዳዩ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96  የሚዳኝ አይደለም በማለት ቢሆንም በበኩላችን ግን በመዝገቡ ከቀረበው  ክርክር አንፃር ምላሽ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ በግራ ቀኙ  መካከል የነበረው ግንኙነት የቅጥር ውል ነው  ወይስ የእውቀት ሥራ ውል ነው? የሚል መሆኑን በመገንዘብ ከዚሁ ጭብጥ  አንፃር  ጉዳዩን መርምረናል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ከተጠሪ  ጋር የስራ ውል ከመሰረቱበት ጊዜ በፊት ጀምሮ የሰራ ግንኙነቱ እስከተቋረጠበት ጊዜ ድረስ ፈቃድ አውጥተው የጥብቅና አገልግሎት በመስጠት ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ  መሆኑንን ተጠሪው በሰበር መልሱ ላይ የገለፀ ሲሆን አመልካችም የተጠሪው ስራ ብዙ በመሆኑ በጥብቅና ፈቃዴ ሌላ ስራ ልሰራ አልቻልኩም ከማለት በስተቀር በጥብቅና  ስራ አገልግሎት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ መሆኑን አላስተባበሉም፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ የስራ ግንኙነት ደግሞ በፍ/ሕ/ቁ.2632-2638  በተመለከተው መሠረት በእውቀት ስራ ውል ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንጂ በአሰሪና  ሰራተኛ ጉዳይ  አዋጅ  ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3(1) እና (2)  መሠረት በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ባለመሆኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 እና 494/98 መሠረት ሰራተኛም ሆነ የሰራ መሪ ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ የግራ ቀኙ መብትና ግዴታም የሚወሰነው ከላይ በተጠቀሱትና አግባብነት የሚኖራቸው ሌሎች የፍ/ብሔር ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 በግራ ቀኙ መካከል ላለው  ግንኙነት ተፈፃሚነት  ሊኖረው አይችልም፡፡ በዚህም  ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶች  ለውሣኔያቸው  የሰጡት  ምክንያት የተሳሳተ ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን ውሳኔው ተገቢ መሆኑን  በመገንዘብ የሚከተለውን ውሳኔ  ሰጥተናል፡

**ው  ሳ  ኔ**

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት  በመ.ቁ.  23650  በ19/08/04  ዓ.ም.  የሰጠው  ውሳኔ  እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት  በመ/ቁ. 119028  በ13/10/04  የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በውጤት ደረጃ ፀንተዋል፡፡
2. በሰበር ደረጃ የደረሰውን ወጪና ኪሣራ  ግራ ቀኙ የየራቸውን ይቻሉ፡፡
3. ክርክሩ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች  ፊርማ አለበት

እ/ብ